# ሴት አግቶ ጀግና ?

የናቴ ልጅ ብለህ ፣ ካንጀት የወደድከው
ትላንት እሱ ሲሞት ፣ ደምህ ደሜ ያልከው
በወገናዊነት ፣ ከፍ ከፍ ያረከው
ሞቱን ልትሞትለት ፣ ከጎኑ የቆምከው
ጠጠር መለሰልህ ፣ ወርቅ ባበደርከው
በዚህ ይሁዳ ነው ፣ ዛሬ የታረድከው ።

በኢትዮጵያ ጠላት ፣ በአረብ ተደግፎ
በግራም በቀኝም ፣ ጠላት አሰፍስፎ
አራጅ ነፍሰ ገዳይ ፣ ሺውን አሰልፎ
ሊወርህ ሲዘጋጅ ፣ ድንበርህን አልፎ
አሻፈረኝ ካለ ፣ ካልተቀመጠ አርፎ
ምነው የማትተም ፣ አትወጣ ከቀፎ ?
እንደምን ይተኛል ፣ ትኋን ተባይ ታቅፎ ።

ጠባብ ተደራጅቶ ፣ ሲያጠቃህ ብቻህን
በግፍ እያረደ ፣ ሚስትና ልጅህን
እያቃጠለልህ ፣ ቤተ ዕምነትህን
እያፈራረሳት ፣ እናት ሐገርህን
አልሰማም እያለ ፣ ስቃይ በደልህን
ምነው አትደራጅ ፣ አንሳ እንጂ ጋሻህን
ተዘጋጅተህ ጠብቅ ፣ ወልውል ጠብመንጃህን
እጅህን አጣምረህ ፣ አትጠብቅ ሞትህን ።

ሞትህን አትጠብቅ ፣ እንግዲህ አማራ
ከምታምነው አምላክ ፣ ከፈጣሪ ጋራ
ክተት ፋኖ ብለህ ፣ ከፍ አርገህ ተጣራ
በጋ የመሰለው ፣ ሃምሌ ስላባራ
ደካማን በመግደል ፣ ቆሞ የሚያቅራራ
የፈሪ ወጉ ነው ፣ ሴት ይዞ ፉከራ ።

መቼም ታሪክህን ፣ ያውቀዋል አይስተው
በደካማዎች ላይ ፣ ዛሬ የተበተው
ያረደውን አርዶ ፣ ሴቶችን ያገተው
የወንድነትን ልክ ፣ አያውቀውምና
ነገ ታየዋለህ ፣ ሱሪው ላይ ሲሸና
ዛሬ ላይ ይፎክር ፣ ሴት አግቶ ጀግና ?

ታዘቢው
February 03 2020